7ኛ ዓመት ቁጥር 22
7th Year No. 22

ባህር ዳር ነሐሴ 4/1994 ዓ/ም
Bahir Dar 10th August 2002

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

ዝክረ ህግ

ZIKRE HIG

Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

1324
ያንዱ ዋጋ ብር 4·70
Unit price ---------

ማውጫ

Contents

አዋጅ ቁጥር 75/1994 ዓ/ም
የጥብቅና ሥራ ፈቃድ አሠጣጥ፣ ምዝገባና የጠበቆችን ስነ-ምግባር ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ

Proclamation No. 75/2002
A Proclamation to provide for the licensing, registration and controlling the code of conduct of Advocates.

አዋጅ ቁጥር 75/1994 ዓ.ም.
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጥብቅና ሥራ ፈቃድ አሰጣጥ፣ ምዝገባና የጠበቆችን ስነምግባር ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ

የጥብቅና አገልግሎት በሕግ ሙያ የሠለጠነ እና በሙያው ሰፊ ልምድ ያለው፣ የፍርድ ቤት አሠራርን ጠንቅቆ የሚያውቅ፣ የታማኝነት፣ የቅንነትና የእውነተኝነት መንፈስን የተላበሰ ሰው፣ ለሕግ የበላይነትና ለፍትሕ መስፈን ከፍትሕ አካላት ጐን በአጋርነት የሚሰለፍበት ሙያ በመሆኑ፣

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍ/ቤቶች ለመስራት የሚችሉ ጠበቆችን ፈቃድ አሰጣጥ፣ ምዝገባና ስነ ምግባር መቆጣጠሪያ ስርዓት በተሟላ መልኩ በሕግ መደንገግ በማስፈለጉ፣

የጥብቅና አገልግሎት የሚሰጡ ሰዎችን የሙያ ብቃት ደረጃ ከሚሰጡት አገልግሎት ጋር የተመጣጠነ ለማድረግና በስራው ለመሠማራት የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

Proclamation No. 75/2002.
The Amhara National Regional State Proclamation to provide for the licensing, registration and controlling the code of conduct of Advocates.

WHEREAS, advocacy is a profession wherein a person trained and experienced in law, fully aware of judicial proceddings and dictated by the spirit of loyalty, sincerity and genuinety and works in cooperation with the judicial organs for the rule of law and prevalence of justice;

WHEREAS, it is deemed essential to regulate exhaustively, the licensing, registration and controlling of the code of conduct of advocates practicing before Regional courts;

WHEREAS, it has become necessary to upgrade the criteria required for practicing advocacy with a view of harmonizing the professional competence of advocates with the services they render;

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በ1994ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣው የክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/ ሥር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ " የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጥብቅና ሥራ ፈቃድ አሠጣጥ፣ ምዝገባና የጠበቆች ሥነ ምግባር መቆጣጠሪያ አዋጅ ቁጥር 75/1994 ዓ.ም " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያስጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "ፍርድ ቤት" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍ/ቤቶችንና ሌሎች ዳኝነት ነክ አካላትን ያጠቃልላል፣
2. "የጥብቅና አገልግሎት" ማለት የገንዘብ ክፍያ በመቀበል ወይም ወደፊት የሚገኝ ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ሲባል ወይም ያለክፍያ ፍ/ቤት ፊት ሊቀርብ የሚችል ማንኛውንም ዓይነት የውል ስምምነት፣ የድርጅት ማቋቋሚያ፣ ማሻሻያ ወይም ማፍረሻ ሰነድ ወይም ለፍ/ቤት የሚቀርብ ሰነድ ማዘጋጀትን፣ ሶስተኛ ወገኖችን በመወከል በፍ/ቤት ፊት ቀርቦ መከራከርን እና ማናቸውንም ዓይነት የሕግ ምክር አገልግሎት መስጠትን ያጠቃልላል፣
3. " ጠበቃ " ማለት የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ለመስጠት ስሙ በመዝገብ የተመዘገበ የሕግ ባለሙያ ነው፣
4. " የሕግ ጉዳይ ፀሐፊ " ማለት የሕግ ምክርና አስተያየትን በመስጠትና ሕግ ነክ ሰነዶችን በማዘጋጀት ጠበቃውን የሚያግዝ ሰው ነው፣

NOW, THERFORE, The Amhara National Regional state Council, in accordance with the power vested in it under sub-article 3/1 of article 49 of the 2001 Revised Regional Constitution, hereby proclaims as follows:

PART ONE

General

1. Short title

This Proclamation may be cited as " The proclamation to provide for the licensing, registration and controlling of code of conduct of advocates practicing before the Amhara National Regional State courts No.75/2002".

2. Definitions

In this proclamation, unless the context requires otherwise:

1. " Court" means the Amhara National Regional Courts and other quasi-judicial organs.
2. " Advocacy Service" means the preparation of contracts, memorandum of association, documents of amendment or dissolution of same, or documents to be adduced in court, litigation before courts on behalf of third parties, and includes rendering any legal consultancy services for consideration or without consideration or for direct or indirect future consideration.
3. " Advocate" means a lawyer whose name is registered in a register in order to render advocacy services.
4. " Law Clerk" means a person who assists an advocate in the drawing up of legal documents and rendering of legal advice.

5. "የጠበቃ ረዳት" ማለት በጠበቃው ስር በመሆን በጠበቃው የተዘጋጁ የክስ ማመልከቻዎችን ለፍርድ ቤት በማቅረብ ፋይል የሚያስከፍት፣ ከፍርድ ቤት የሚወጡ መጥሪያዎችን፣ ትእዛዞችን እና የፍርድ ግልባጮችን በማውጣት ለሚመለከታቸው ሰዎች የሚያደርስ ሰው ነው፣

6. "ደንበኛ" ማለት ስለራሱ ወይም ስለሌላ ሰው ጉዳይ ማንኛውንም የጥብቅና አገልግሎት ለማግኘት ከጠበቃ ጋር የተዋዋለ ወይም የጉዳዩን ፍሬ ነገር ለጠበቃ ያስረዳ ሰው ነው፣

7. "ቢሮ" ወይም "ቢሮ ኃላፊ" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትሕ ቢሮ ወይም የዚሁ ቢሮ ኃላፊ ነው፣

8. "መዝገብ" ማለት ጠበቆች የሚመዘገቡበትና በቢሮው የሚጠበቅ ሪከርድ ነው፣

9. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፣

10. "ሁለተኛ ደረጃ የጥብቅና ሥራ ፈቃድ" ማለት በክልሉ ውስጥ በወረዳ ፍርድ ቤትና ከዚያ በታች ባሉ ሌሎች ዳኝነት ሰሚ አካላት ፊት የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ፈቃድ ነው፣

11. " አንደኛ ደረጃ የጥብቅና ሥራ ፈቃድ" ማለት በማናቸውም የክልሉ ፍርድቤቶችና ሌሎች ዳኝነት ሰሚ አካላት ፊት በክልል ነክ ጉዳዬች የጥብቅና አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ፈቃድ ነው።

ክፍል ሁለት

ስለ ፈቃድ አሰጣጥ ሁኔታና ስለጠበቆች ምዝገባ

3. ፈቃድ ስለማስፈለጉ

1. በአማራ ብሔራዊ ክልል የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልግ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የጥብቅና ሥራ ፈቃድ ሊኖረው ይገባል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው ቢኖርም የሚከተሉት ሰዎች ያለ ጥብቅና ሥራ ፈቃድ አገልግሎት መስጠት ይችላሉ፦

5. " Advocate Assistant" means a person whom, under the guidance of an advocate, opens files or claims prepared by the advocate in the court of law and receives summons, orders and copies of judgments from courts and delivers it to the concerned persons.

6. " Client" means a person who enters into contracts with an advocate to obtain advocacy services for him or for a third party or who tells the facts of the case to an advocate;

7. " Bureau" or "Bureau Head" means the Justice Bureau or the Justice Bureau Head of the Amhara National Regional State respectively;

8. " Register" means a record wherein advocates are registered and kept by the Bureau;

9. " Person" means any natural or juridical person;

10. " Second class advocacy license" means an advocacy license which enables an advocate to render advocacy services before woreda courts and other lower quasi-judicial organs of the region;

11. " First class advocacy license" means an advocacy license which enables an advocate to render advocacy services before all courts and quasi-judicial organs of the region.

PART TWO

Licensing and Registration of Advocates

3. Requirement of License

1. Any Ethiopian who wishes to render advocacy services in the Amhara National Regional State shall hold a license.

2. Notwithstanding the provisions of sub article (1) of this Article, the following persons may render advocacy services without a license:

ሀ. ስለ ራሱ ጉዳይ የሚከራከር ሰው፣

ለ. ያለ ክፍያ ለትዳር ጓደኛው፣ ለወላጆቹ፣ ለልጆቹ፣ ለአያቶቹ፣ ለእህቱም ሆነ ለወንድሙ እንዲሁም ሞግዚት ወይም አሳዳሪ ለሆነለት ሰው የሚከራከር ሰው፣

ሐ. የግል ድርጅትን ወይም የንግድ ማኅበርን በፍርድ ቤት ለመወከል ስልጣን ተሰጥቶት የድርጅቱን ወይም የኩባንያውን ጉዳዮች በሚመለከት የሚከራከር ማንኛውም የድርጅት ኃላፊ ወይም ሸሪክ፣

መ. የመንግስት መስሪያ ቤትን ወይም የልማት ድርጅትን በሚመለከት የሚከራከር ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የልማት ድርጅት ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ወይም በእርሱ የተወከለ ሰው፣

ሠ. ማንኛውም የሠራተኛ ማኅበር መሪ ወይም ማኅበሩ የሚወክለው ሰው።

4. <u>ፈቃድ ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>

1. የጥብቅና ሥራ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ ለዚሁ ተግባር በቢሮው በተዘጋጀ ቅጽ ተሞልቶ ይቀርባል።

2. አመልካቹ ከማመልከቻው ጋር የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ ይኖርበታል:-

ሀ. የትምህርት ማስረጃ፣

ለ. ከቀድሞ አሠሪው ስለ ስነ ምግባሩ ወይም ስለ ስራ አፈጻጸሙ የሚገልጽ ደብዳቤ፣

ሐ. ፈቃድ ለማግኘት የሚሰጠውን የሙያ መግቢያ ፈተና ማለፉን የሚያሣይ ማስረጃ፣

a. A person who pleads his own case;

b. A person who pleads, without payment, the cases of his/her spouse, parents, children, grandparents, sisters, brothers or of a person to whom he is a tutor or guardian;

c. A head or a shareholder or a partner of a private organization or company who pleads the case of the organization or company holding a power of attorney to represent such organization or company in court;

d. An official of a public body or a public enterprise or a person designated by him who pleads the actions of such public body or public enterprise.

e. Any trade union leader or a person designated by the union.

4. <u>Application for license</u>

1. An application for advocacy license shall be made in a form designed for such purpose by the bureau.

2. The applicant shall submit the following documents together with his/her application:

a. Credentials;

b. A letter from his/her former employer regarding the applicant's conduct or performance;

c. Evidence showing that the applicant has passed the entry examination set for the license he/she applies for;

መ. የፈቃድ ክፍያ መፈጸሙን የሚያሣይ ማስረጃ፤

ሠ. ሌሎች በቢሮው የሚጠየቁ ማስረጃዎች።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ /ሐ/ የሚቀርብ የምስክር ወረቀት ዋጋ የሚኖረው ፈተና ማለፉ በታወቀ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከቀረበ ብቻ ይሆናል።

5. ፈቃድ ስለመስጠት

1. ቢሮው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 መሠረት የጥብቅና ሥራ ፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻ ተሟልቶ ሲቀርብለት ከ30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ተገቢውን ውሣኔ መስጠት አለበት።
2. በፈቃዱ ላይ የሚጠቀሰው ፍሬ ጉዳይ የሚከተሉትን የሚያካትት ይሆናል:-

   ሀ. የጠበቃውንሙሉ ስምና ዜግነት፤

   ለ. መደበኛ የመኖሪያና የሥራ አድራሻ፤

   ሐ. የፈቃዱን ዓይነት፤

   መ. የፈቃድ ሰጭውን ስምና ፊርማ።
3. ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ቢኖሩም ቋሚ ስራ ላለው ሰው የጥብቅና ፈቃድ አይሰጥም።

6. ስለ ፈቃድ እድሳት

1. የጥብቅና ሥራ ፈቃድ በየዓመቱ መታደስ አለበት።
2. ፈቃድ ለማሳደስ የሚቀርብ ማመልከቻ ፈቃዱ የሚያገለግልበት የአንድ ዓመት ጊዜ ከማለቁ ከአንድ ወር በፊት መቅረብ አለበት።
3. አመልካቹ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ መሠረት የማሳደሻ ክፍያ ይከፍላል።

d. Evidence showing that the applicant has paid the required fee;

e. Such other information required by the Bureau.

3. A certificate produced in accordance with sub article 2(c) of this Article shall be valid only where it is produced within one year as of the date of knowledge of passing the exam.

5. Issuance of License

1. Where the Bureau finds that the application made for a license is in full compliance with the provisions of Article 4 of this proclamation, it shall render its decision within a period of not more than thirty days.
2. The license shall include the following particulars:

   a. The name and nationality of the advocate;

   b. Addresses of the advocate's residence and place of business;

   c. Type of license;

   d. Name and signature of the issuing Officer.
3. Notwithstanding the provisions above, a license may not be issued to a person who has another permanent job.

6. Renewal of License

1. A license shall be renewed annually
2. An application for renewal of license shall be submitted one month before the expiry of the one-year period for which it is issued.
3. An applicant shall pay the renewal fee determined by a regulation to be issued with this proclamation.

7. <u>የፈቃድ ዓይነቶች</u>

በቢሮው የሚሰጡ ሁለት ዓይነት የጥብቅና ሥራ ፈቃዶች ሲኖሩ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው:-

ሀ. 2ኛ ደረጃ የጥብቅና ሥራ ፈቃድ፣ እና

ለ. 1ኛ ደረጃ የጥብቅና ሥራ ፈቃድ::

8. <u>ሁለተኛ ደረጃ የጥብቅና ሥራ ፈቃድ</u>

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ያሟላ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ 2ኛ ደረጃ የጥብቅና ሥራ ፈቃድ ይሰጠዋል:-

1. ከታወቀ የሕግ ትምህርት ቤት በዲፕሎማ የተመረቀ እና በሙያው ቢያንስ ሁለት ዓመት የሠራ ወይም በሕግ የሥልጠና ፕሮግራም በሰርተፊኬት ተመርቆ፣ በዳኝነት፣ በዐቃቤሕግነት፣ በሬጅስትራርነት ወይም በነገረ ፈጅነት ቢያንስ ለአምስት ዓመት ያገለገለ፣
2. ለፍትሕ ሥራ አካሄድ መልካም ስነ ምግባር ያለው፣
3. ለደረጃው የሚሰጠውን የጥብቅና መግቢያ ፈተና ያለፈ፣
4. ምግባረ ብልሹነትን በሚያመለክት ወንጀል ተከሶ ያልተቀጣ::

9. <u>አንደኛ ደረጃ የጥብቅና ሥራ ፈቃድ</u>

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ያሟላ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ አንደኛ ደረጃ የጥብቅና ሥራ ፈቃድ ይሰጠዋል:-

1. ከታወቀ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም በሕግ ዲግሪ የተመረቀ፣ የኢትዮጵያን መሠረታዊ ሕጎች የሚያውቅና በሙያው ቢያንስ የአራት ዓመት የሥራ ልምድ ያለው፣
2. ከታወቀ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም በሕግ ዲፕሎማ የተመረቀ፣ የኢትዮጵያን መሠረታዊ ሕጎች የሚያውቅና በሙያው ቢያንስ የስምንት ዓመት ልምድ ያለው፣

7. <u>**Types of License**</u>

There shall be two types of license to be issued by the Bureau:

a. Second Class advocacy license; and

b. First Class advocacy license.

8. <u>**Second Class Advocacy License**</u>

Any Ethiopian who fulfills the requirements specified hereinunder shall be issued with a second class advocacy license:

1. Where he has a diploma in law from a legally recognized law school and has a minimum of two years relevant experience; or has a minimum of five years experience as a judge, or public prosecutor, or registrar, or public pleader, after obtaining certificate in law;
2. Whose code of conduct is suitable for assisting in the proper administration of justice;
3. Who has passed the advocacy entrance examination set for the license applied for;
4. Who is not convicted and sentenced in an offence showing an improper conduct.

9. <u>**First Class Advocacy License**</u>

Any Ethiopian who fulfills the requirements specified hereinunder shall be issued with a first class advocacy license:

1. Where he has a degree in law from a legally recognized educational institution, knows the basic laws of Ethiopia and has a minimum of four years relevant experience;
2. Where he has a diploma in law from a legally recognized educational institution, knows the basic laws of Ethiopia and has a minimum of eight years relevant experience;

3. ለፍትሕ ስራ አካሄድ መልካም ስነ ምግባር ያለው፣

4. ለደረጃው የሚሰጠውን የጥብቅና መግቢያ ፈተና ያለፈ፣

5. ምግባረ ብልሹነትን በሚያመለክት ወንጀል ተከሶ ያልተቀጣ::

10. ለጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና ስለመቀመጥ

1. ማንኛውም የ2ኛ ደረጃ ጥብቅና ሥራ ፈቃድ እንዲሰጠው የሚጠይቅ አመልካች በቢሮው ለደረጃው የሚዘጋጀውን የጥብቅና ሥራ ፈቃድ ፈተና መውሰድ አለበት::

2. አንደኛ ደረጃ ጥብቅና ሥራ ፈቃድ እንዲሰጠው የሚጠይቅ ማንኛውም አመልካች ጥያቄውን ያቀረበው ስራውን ከለቀቀ ከሁለት ዓመት በኋላ የሆነ እንደሆነ በቢሮው ለደረጃው የሚዘጋጀውን ፈተና የመውሰድ ግዴታ አለበት::

11. ቃለ መሐላ ስለመፈጸም

ማንኛውም ፈቃድ የሚሰጠው ጠበቃ የሚከተለውን ቃለ መሐላ በጽሁፍ ያረጋግጣል፣

እኔ ---------- ዛሬ --------- ቀን ------- ዓ.ም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትሕ ቢሮ የጥብቅና ፈቃድ ስቀበል በሙያዬ በቅንነትና በታማኝነት በመስራት የምወክላቸውን የደንበኞቼን ጥቅም ሕግ በሚፈቅደው መጠን ላስከብር፣ ከተከራካሪዎችና ከሙያ ባልደረቦቼ ጋር በመግባባት ልሠራ እና ለፍርድ ቤቶች ተገቢውን ክብር በመስጠት ለሕግ መከበር አጋዥ ለመሆን ቃል እገባለሁ::

12. ፈቃድ ስለመመለስ

1. ማንኛውም ጠበቃ ከሙያው ውጭ በሆነ ሥራ በዋናነት የተሰማራ እንደሆነ ወይም በሌላ በማናቸውም ምክንያት ሙያዊ አገልግሎት ለመስጠት ያልቻለ እንደሆነ ፈቃዱን እንደሁኔታው ለተወሰነ ጊዜ ወይም በቋሚነት ለቢሮው ይመልሳል::

3. Whose code of conduct is suitable for assisting in the proper administration of justice;

4. Who has passed the advocacy entrance examination set for the license applied for;

5. Who is not convicted and sentenced in an offense showing an improper conduct.

10. Sitting for Advocacy Entrance Examination

1. An applicant for Second Class advocacy license shall take an examination set by the bureau for same type of license.

2. An applicant for First Class advocacy license shall be obliged to take an examination set by the Bureau for same type of license where he applies after a period of two years from the termination of his employment.

11. Taking an Oath

Any advocate shall take in writing the following Oath:

I, when taking this license from the Amhara National Regional State Justice Bureau, this Day of ------ 19----- promise that I will, With honesty and good faith defend the cases of my clients in accordance with the law, work with understanding with my opponents and colleagues, and give due respect to courts and be helpful for/to the rule of law.

12. Returning a License

1. Any advocate shall return his license to the bureau temporarily or permanently, as the case may be, where he is mainly engaged in an activity outside his profession or is not in a position to render his services on any other ground.

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ፈቃዱን የመለሰ ጠበቃ ፈቃዱን እንዲመልስ ያስገደደው ምክንያት እንዳበቃ ወይም እንደተወገደ ከስራው ተለይቶ በቆየበት ጊዜ በስነ ምግባር ጉድለት ሊያስጠይቀው የሚችል ጥፋት ካልፈፀመ በስተቀር ፈቃዱን ሊወስድ ይችላል::

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ፈቃዱ እንዲመለስለት ጥያቄውን ያቀረበው ስራውን ከተወ ከሁለት ዓመት በኋላ የሆነ እንደሆነ በቢሮው ለደረጃው የሚዘጋጀውን ፈተና እንደ አዲስ መውሰድ አለበት::

13. ፈቃድ ስለማገድ ወይም ስለመሰረዝ

1. ይህንን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን የጣሰ ማናቸውም ጠበቃ እንደሁኔታው ፍቃዱ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል::

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ቢሮው ከሚከተሉት ሁኔታዎች በአንዱ ፈቃዱን ሊሰርዝ ይችላል:-

    ሀ. ፈቃዱ የተገኘው በማታለል ወይም የሀሰት ማስረጃ ወይም መግለጫ በማቅረብ እንደሆነ፣

    ለ. ለጥብቅና ሙያ ብቃት ተገቢነት የሌለው መሆኑን በሚያሣይ የወንጀል ድርጊት ተከሶ ጥፋተኝነቱ የተረጋገጠ እንደሆነ፣

    ሐ. ከተሰጠው የጥብቅና ሥራ ፈቃድ ደረጃ በላይ ሲሰራ የተገኘ እንደሆነ፣

    መ. በማንኛውም ዓይነት የማጭበርበር ድርጊት ወይም የሙያ ሥነ ምግባር ድንጋጌዎችን በከባድ ሁኔታ በመተላለፍ የጥብቅና ሥራ ማካሄዱ የተረጋገጠ እንደሆነ፣

    ሠ. ከጥብቅና ሙያ በታገደበት ወቅት የጥብቅና ሙያ አገልግሎት መስጠቱ የተረጋገጠ እንደሆነ፣

2 An advocate who has returned his license in accordance with sub article (1) of this Article may retake same upon termination or removal of the cause which compelled him to return his license, provided that he has not committed any fault which would make him liable for breach of discipline.

3 The applicant shall take an examination set by the bureau for the type of license in accordance with sub article 2 of this Article if he applies two years following termination of Advocacy.

13. Suspension or Revocation of License

1. A license may be suspended or revoked, as the case may be, where an advocate violates regulations and directives issued in accordance with this proclamation.

2. Without prejudice to the generality of sub-article (1) of this Article, the bureau may revoke a license on one of the following grounds:

    a. Where the license is obtained with fraud /deceit or by producing falsified document or information;

    b. Where the advocate is charged with an offense showing his incompetence to continue practicing and found guilty thereof;

    c. Where the advocate is found practicing in a court for which he is not licensed;

    d. Where it is ascertained that he is found practicing by any sort of deceitful activity or in a gross transgression of Advocates' Ethical regulation;

    e. Where he is found practicing advocacy while suspended;

734 758

ረ. ለራሱ ወይም ለሌላ ጠበቃ በአገናኝ አማካይነት የጥብቅና ስራ ለማስገኘት ገንዘብ የሰጠ ወይም ለመስጠት የሞከረ እንደሆነ፣

ሰ. ከጥብቅና ሙያ ጋር በግልጽ የሚጋጭ ወይም የማይጣጣም ተጨማሪ ስራ ሲያከናውን የተገኘ እንደሆነ።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ቢሮው ከሚከተሉት ሁኔታዎች በአንዱ ፈቃዱን ሊያግድ ይችላል፡-

ሀ. ያለበቂ ምክንያት ፈቃዱን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 መሠረት ያላሳደሰ እንደሆነ፣

ለ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15 /2/ የተመለከተውን በመተላለፍ የሕግ ጉዳይ ፀሐፊ ወይም የጠበቃ ረዳት አድርጐ የሠራ እንደሆነ።

14. ስለ መመዝገብ

1. ፈቃድ የተሰጠውን ጠበቃ ስምና ዜግነት፣ የፈቃድ ዓይነት መደበኛ የስራ አድራሻው እና ሌሎች በቢሮው የሚጠየቅ አስፈላጊ መረጃዎች የሚይዝ መዝገብ ይኖረዋል።
2. ስሙ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/1/ ስር በተመለከተው መዝገብ ውስጥ ያልገባ ሰው የጥብቅና አገልግሎት መስጠት አይችልም።
3. መዝገቡ ለሕዝብ ግልጽ ይሆናል።

15. ከጠበቃው ጋር የሚሰሩ ሰዎችን ስለመመዝገብ

1. ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና አገልግሎት ድርጅት በስራው የሚያግዙትን የሕግ ጉዳይ ፀሐፊዎች፣ የጠበቃ ረዳቶች፣ ፀሐፊዎች፣ ሌሎች ሠራተኞች ስም እና የስራ ኃላፊነት ቢሮው ለዚህ ጉዳይ ለመደበው ባለስልጣን በጽሁፍ በማሳወቅ ያስመዘግባል።
2. ማንኛውም ጠበቃ ከቢሮው ወይም በእርሱ ከተወከለ ባለስልጣን ፈቃድ ሳያገኝ፡-

f. Where he gives or attempts to give money to a person with a view of securing a job for himself or another advocate, through intermediary;

g. Where he carries out additional activity which is obviously conflicting or inconsistent with his profession.

3. Without prejudice to the generality of sub article (1) of this Article, the Bureau may suspend a license on one of the following grounds:

a. Where he fails, without good cause, to renew his license in accordance with Article 6 of this proclamation;

b. Where he employs persons not permitted to practice as a law-clerk or advocate assistant in violation of sub-article (2) of Article 15 of this proclamation.

14. Registration

1. There shall be a register in which the name and nationality of the advocate, license type, normal residence and usual place of business of the advocate and such other particulars required by the bureau are registered.
2. No person may render advocacy service unless he is registered in the register specified in sub-article (1) of this Article.
3. The Register shall be open to the public.

15. Registration of Persons Working with the Advocate

1. Any advocate or a law firm shall notify in writing to an official assigned by the bureau for registration of the names and responsibilities of secretary typists, law-clerks, assistant advocates and other employees working under his supervision.
2. Any advocate may not, without a prior consent of the bureau or an official designated, employ the following persons as an assistant advocate or a law clerk:

ሀ. ከመዝገብ ስሙ የተፋቀን፣

ለ. ከጥብቅና ሙያ አገልግሎት የታገደን፣

ሐ. በዲሲፕሊን ጥፋት ምክንያት ከመ/ቤቱ የተባረረን ሰው፣

መ. ምግባረ ብልሹነትን በሚያመለክት ወንጀል ተከስሶ የተፈረደበትን ወይም፣

ሠ. በመንግስት ስራ ተቀጥሮ የሚሰራን ሰው፣ በጠበቃ ረዳትነት ወይም በሕግ ጉዳይ ፀሐፊነት መቅጠር አይችልም።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የሕግ ትምህርት ወይም ስልጠና ወይም ልምድ የሌለው ሰው በሕግ ጉዳይ ፀሐፊነት ሊቀጠር አይችልም።

ክፍል ሦስት

አስፈጻሚ አካላት

16. የቢሮው ስልጣንና ተግባር

ቢሮው፡-

1. የጥብቅና ሥራ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሣል፣ ያግዳል፣ ይሠርዛል፣ ጠበቆችን ይመዘግባል፤
2. ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ መሠረት ክፍያዎችን ያስከፍላል።

17. ስለ ጥብቅና ሥራ ፈቃድ ገምጋሚና የጠበቆች የችሎታና ብቃት መለኪያ ቦርድ

1. የጥብቅና ሥራ ፈቃድ ገምጋሚና የጠበቆች ችሎታና ብቃት መለኪያ ቦርድ /ከዚህ በኋላ "ቦርዱ" እየተባለ የሚጠራ/ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. ቦርዱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ. በቢሮው የሚወከሉ ሁለት ሰዎች፣

ለ. ከክልሉ ጠበቆች ማህበር ሁለት ተወካዮች፣

ሐ. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተወካይ፣

a. A person whose name is deregistered;

b. A person suspended from practicing advocacy;

c. A person dismissed from office due to discipilinary infringement;

d. A person charged for and convicted in an offense of improper conduct; or

e. A public servant.

4. Without prejudice to the provisions of sub article (2) of this Article, a person who has no legal education, training or experience may not be employed as a law-clerk.

PART THREE

Executive Organs

16. Powers and Duties of the Bureau

The Bureau shall:

1. Issue, renew, suspend or revoke licenses as well as register advocates.
2. Charge fees, determined by the regulation to be issued in accordance with this proclamation for the service it renders.

17. License Evaluating and Advocates' capacity Assessment Board

1. License Evaluating and Advocates' capacity assessment board hereinafter referred to as "the Board" is established by this proclamation.
2. The Board is composed of the following members:

a. Two representatives of the Bureau;

b. Two representatives of the advocates' Association;

c. A representative of the Regional Supreme Court;

መ. የባሕርዳር ዩኒቨርስቲ ሕግ ትምህርት ክፍል ተወካይና

ሠ. በቢሮ ሀላፊው ተመርጠው የሚሰየሙ ሌሎች ሁለት አባላት::

3. የአንድ አባል የአገልግሎት ዘመን ሁለት አመት ሲሆን የቦርዱ ሰብሣቢ ከአባላቱ መካከል በቢሮ ሀላፊው ይሰየማል::

4. በዚህ አዋጅ መሠረት የጠበቆች ዲሲፕሊን ጉባዔ አባል የሆነ ማንኛውም ሰው የቦርዱ አባል ሊሆን አይችልም::

18. <u>የቦርዱ ስልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ ተጠሪነቱ ለቢሮው ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. የአመልካቹን ማስረጃዎች መርምሮ አመልካቹ ፈቃድ እንዲሰጠው ወይም እንዳይሰጠው ለቢሮ ሀላፊው የውሣኔ ሀሣብ ያቀርባል፣

2. አመልካቹ ለፍትሕ ስራ አካሄድ የሚስማማ የስነ ምግባር ብቃት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ ማንኛውንም ሰው ጠርቶ መጠየቅ ወይም ማስረጃ አስቀርቦ መመርመር ይችላል፣

3. ከቢሮ ሀላፊው ወይም በእርሱ ከሚወከል ባለስልጣን ጋር በመመካከር በየአመቱ የጥብቅና ችሎታ መመዘኛ ፈተና እያዘጋጀ በተወሰነ ጊዜና ቦታ ለአመልካቾች ይሰጣል፣

4. የፈተና ወረቀቶችን ያርማል፣ ለማለፊያ የሚያበቃውን ነጥብ ይወስናል፣ የፈተናውን ውጤት ለቢሮ ሀላፊው ወይም በእርሱ ለሚወከል ባለስልጣን አቅርቦ ሲፀድቅ ውጤቱን በይፋ ያስታውቃል፣

5. ስለ ስራው አፈጻጸም የስነ ስርዓት መመሪያ አዘጋጅቶ ለቢሮው ያቀርባል ሲፀድቅም በስራ ላይ ያውላል::

19. <u>ስለቦርዱ ስብሰባ</u>

1. ቦርዱ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፣

d. A representative of the Law department of Bahir Dar University; and

e. Two members designated by the head of the Bureau.

3. The term of office of a member of the board shall be two years and the chairperson of the board shall be designated by the Head of the Bureau from among the members.

4. Any member of the Advocates' Discipilinary council pursuant to this proclamation, may not become a member of the Board.

18. <u>Powers and Duties of the Board</u>

The Board is accountable to the Bureau and shall have the following powers and duties:

1. Shall submit, after examining the supporting documents produced by the applicant, a recommendation to the Head of the Bureau as to whether the applicants shall be issued with a license or not.

2. May cause the production of any witness or evidence and examine same with a view to ascertaining the suitability of the advocate's character in assisting the administration of justice.

3. Shall prepare and give advocacy entrance exams to applicants at a fixed time and place, in consultation with the Head of the Bureau or an official delegated by him.

4. Shall mark exam papers, determine the pass mark and publicize the result after submitting it for approval to the Head of the Bureau or an official delegated by him.

5. May issue and submit to the Head of the Bureau its own rules of procedure and implement same upon approval.

19. <u>Meetings of the Board</u>

1. The Board shall conduct meetings as frequently as required.

2. የቦርዱ አባላት ሁለት ሶስተኛው ከተገኙ ምልዐተ ጉባዔ ይሆናል፣

3. የቦርዱ ውሣኔዎች በስብሰባው በተገኙ አባላት በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፣ ሆኖም ድምጹ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ወሣኝ ድምጽ ይኖረዋል፣

4. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀፅ 1 እስከ ንዑስ አንቀፅ 3 የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ስነ ስርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል::

20. ስለጠበቆች ዲስፕሊን ጉባዔ

1. የክልሉ ጠበቆች ዲስፕሊን ጉባዔ /ከዚህ በኋላ "ጉባዔው" እየተባለ የሚጠራ/፣ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል::

2. ጉባዔው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል:-

   ሀ. የቢሮው ሁለት ተወካዮች፣

   ለ. የክልሉ ጠበቆች ማህበር ሁለት ተወካዮች፣

   ሐ. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተወካይ::

3. የአንድ አባል የአገልግሎት ዘመን ሁለት ዓመት ሲሆን የጉባዔው ሰብሣቢ ከአባላቱ መካከል በቢሮ ኃላፊው ተመርጦ ይሰየማል::

4. በዚህ አዋጅ መሠረት የቦርድ አባል የሆነ ማንኛውም ሰው የጠበቆች ዲስፒሊን ጉባዔ አባል ሊሆን አይችልም::

21. የጉባዔው ስልጣንና ተግባር

የጉባዔው ተጠሪነት ለቢሮው ሆኖ:-

1. ይህንን አዋጅ በመተላለፍ በጠበቃ ላይ የሚቀርብን ክስ ተቀብሎ ያጣራል፣ ይመረምራል፣

2. በጠበቃ ላይ የቀረበውን ክስ ለማየት የሚያበቃ ማስረጃ መኖሩን ሲያረጋግጥ ጠበቃው መልሱን በ30 ቀናት ውስጥ እንዲያቀርብ መጥሪያው ላይ በመግለጽ ክሱን ለጠበቃው ይልካል፣

2. There shall be a quorum where two-thirds of the members are present.

3. Decisions of the Board shall be passed by a majority vote of members present at a meeting. In case of tie; however, the chairperson shall have a casting vote.

4. Without prejudice to the provisions of this Article, the Board may draw up its own rules of procedure.

20. Advocates' Disciplinary Council

1. Advocates' Disciplinary council /herein after referred to as "Council" / is established by this proclamation.

2. The Council is composed of the following members:

   a. Two representatives of the Bureau;
   b. Two representatives of the Advocates' Association;
   c. A representative of the Regional Supreme Court;

3. The term of office of a member of the council shall be two years and the chairperson of the council shall be designated by the Head of the Bureau from among the members thereof.

4. Any member of the Board, Pursuant to this proclamation, may not become a member of the Council.

21. Powers and Duties of the council

The council is accountable to the Bureau and:

1. Shall investigate a charge brought against an advocate violating the provisions of this proclamation;

2. Shall, where it ascertains that there is adquate evidence to entertain the charge, to the advocate notifying in the summons to appear with his reply within 30 days;

3. በጠበቃው ላይ የቀረበውን ክስና ማስረጃ እንዲሁም በጠበቃው በኩል የተሰጠውን መልስና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ:-

   ሀ. ክሱ ተገቢ ካልሆነ ወይም በበቂ ማስረጃ ካልተደገፈ በመሰረዝ ጠበቃው በነፃ እንዲሰናበት፣

   ለ. ክሱ ተገቢና በማስረጃ የተደገፈ ከሆነ እንደጥፋቱ ክብደት:-

      1. ጠበቃው የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠው፣
      2. ጠበቃው ከአምስት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ከስራው እንዲታገድ፣
      3. ከብር 10000 /አስር ሽህ ብር/ ያልበለጠ የገንዘብ ቅጣት እንዲጣልበት፣
      4. ፈቃዱ ተሰርዞ ስሙ ከመዝገብ እንዲፋቅ፣ ወይም፣
      5. ተገቢ ናቸው ያላቸውን ሌሎች እርምጃዎች እንዲወስድ ለቢሮ ኃላፊው የውሣኔ ሀሣብ ያቀርባል::

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ መሠረት ተገቢው ውሣኔ እስኪሰጥ ድረስ የጥብቅና ስራ ፈቃዱ ለጊዜው ታግዶ እንዲቆይ ሊወስን ይችላል::

5. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በጠበቃው ላይ የሚጣለውን የቅጣት መጠን ለመወሰን የወንጀል ሪኮርድ፣ የጠበቃውን የግል ማኅደር ወይም ሌላ ተመሣሣይ ማስረጃ ማስቀረብ፣ ማስማትና መመርመር ይችላል::

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ /ለ/ መሠረት የተሰጠው ማንኛውም ውሣኔ በጠበቃው የግል ማኅደር ውስጥ እንዲመዘገብ ያደርጋል::

7. በክልሉ ውስጥ የጠበቆች የስነ ምግባር ብቃት የሚጐለብትበትን እና የጥብቅና ሙያ ክብር የሚጠበቅበትን ሁኔታ እያጠና ለቢሮው ሀሣብ ያቀርባል::

3. Shall submit, after examining the charge brought and evidence produced against the advocate and the advocate's reply and evidence thereto, the following recommendations to the Head of the Bureau:

   a. Acquital of the advocate, by dismissing the charge, where the charge is improper or is not supported by evidence;

   b. Where the charge is proper and supported by evidence according to the gravity of the offense:

      1 A written warming to be given to him;
      2 To suspend him for a period of not more than five years;
      3 To impose a fine not exceeding birr 10000 / Ten Thousand Birr/;
      4 To revoke his license and cause the removal of his name from the register; or
      5 To give such other appropriate recommendations to the Head of the Bureau;

4. May temporarily suspend the license until such time that an appropriate decision is given as per sub article (3) of this Article.

5. May examine, where deemed necessary, the antecedents and personal file of the advocate or any other similar evidences in determining the magnitude of penalty to be imposed.

6. Shall cause the recording of any decision approved by the Head of the Bureau as per sub article (3) (b) of this Article in to the personal file of the advocate.

7. Shall undertake studies and submit recommendations to the Bureau on ways of enhancing and the observance of professional conduct.

8. ማንኛውም ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ የመጨረሻ የውሣኔ ሀሣብ ለቢሮው ያቀርባል:: በዚህ ጊዜ ውስጥ ጉዳዩን ለማጠናቀቅ የማይቻልበት በቂ ምክንያት ሲያጋጥም ምክንያቱን በጽሁፍ በመግለጽ ከአርባ አምስት ቀናት የማይበልጥ ተጨማሪ ጊዜ እንዲፈቀድለት የቢሮ ኃላፊውን በጽሁፍ መጠየቅ ይችላል::

22. ስለጉባዔው ስብሰባ

1. ጉባዔው እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ጊዜ መሰብሰብ ይችላል፤
2. ከጉባዔው አባላት መካከል ሁለት ሶስተኛው ከተገኙ ምልዐተ ጉባዔ ይሆናል፤
3. የጉባዔው ውሣኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጹ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሣቢው ያለበት ወገን የጉባኤው ውሳኔ ሆኖ ያልፋል፤
4. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀፅ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 3 የሰፈሩት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ጉባዔው የራሱን የስብሰባ ስነ ስርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል::

23. የቢሮ ኃላፊው ስልጣን

1. የቢሮ ኃላፊው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ 1ና አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌዎች መሠረት እንደአግባብነቱ ከቦርዱ ወይም ከጉባዔው የቀረበውን የውሣኔ ሀሣብ ከመረመረ በኋላ ተገቢውን ውሣኔ ይሰጣል፤
2. ቦርዱ ወይም ጉባዔው በአግባቡ ያላጣራው ወይም ያላጤነው ፍሬ ነገር ወይም ማስረጃ ከተገኘ ይኸው ተጣርቶ ወይም ተገናዝቦ እንዲቀርብለት ለቦርዱ ወይም ለጉባዔው ለአንድ ጊዜ መመለስ ይችላል፤
3. ቦርዱ ወይም ጉባዔው በቢሮ ሀላፊው ጉዳዩ ከተመለሰለት በኋላ በሰላሣ ቀናት ውስጥ ጉዳዩን አጣርቶ ውጤቱን ያቀርባል::

8. Shall submit to the Head of the Bureau a recommendation regarding the final decision on any charge within a period not exceeding three month. Where there are sufficient grounds for failing to dispose of the case within such time, the council may request the Head of the Bureau in writing for an additional time not exceeding forty five days stating the reasons therein.

22. Meetings of the council

1. The council shall conduct meetings as frequently as required.
2. There shall be a quorum where two-thirds of the members are present.
3. Decisions of the council shall be passed by majority vote of members present at a meeting. In case of a tie; however, the chairperson shall have a casting vote.
4. Without prejudice to the provisions of this article, the council may draw up its own rules of procedure.

23. Powers of the Head of the Bureau

1. The Head of the Bureau shall, after considering the recommendations submitted by the board of the council in accordance with sub article (1) of Article 18 and sub article (3) of Article 21, respectively, decide as appropriate.
2. He may for once, direct the recommendation for reconsideration by the board or the council where he is of the opinion that certain facts or evidences have not been considered by it.
3. The Board or the Council may, after examining the case directed to it by the Head of the Bureau, submit the result with in thirty days.

24. <u>በቢሮ ኃላፊው ውሣኔ ላይ ስለሚቀርብ ይግባኝ</u>

1. ቢሮ ኃላፊው የሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ከተገኘ፣ በውሣኔው ቅር የተሰኘ ማንኛውም ወገን ውሣኔው በደረሰው በሰላሣ ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፤
2. ፍርድ ቤቱ ወደ ፍሬ ነገሩ ሣይገባ በሕግ ጉዳይ ላይ ውሣኔ በመስጠት ጉዳዩን ወደ ቢሮ ኃላፊው ይመልሰዋል፤
3. የቢሮ ኃላፊው ውሣኔ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ከተገኘ ቢሮ ኃላፊው የፍርድ ቤቱን ውሣኔ መሠረት በማድረግ ጉዳዩን ያስፈጽማል፡፡

<u>ክፍል አራት</u>

<u>ስለ ጠበቆች ሥነ ምግባርና ስለሚመራባቸው መርሆች</u>

25. <u>አጋዥ እንጅ ችግር ፈጣሪ አለመሆን</u>

ማንኛውም ጠበቃ ሕግን ለማስከበርና ፍትሕን ለማስገኘት የፍትሕ አስተዳደሩን የማገዝ ኃላፊነት አለበት፡፡ ማንኛውም ጠበቃ በተለይም ለደንበኛው ለሌሎች የሕግ ሙያተኞችና ተከራካሪ ወገኖችና ለፍርድ ቤት፣ ለሙያውና በአጠቃላይ ለሕብረተሰቡ ያለበትን የሙያ ኃላፊነት በቅንነት፣ በታማኝነትና በእውነተኛነት መወጣት አለበት፡፡

26. <u>ደንበኛን ስለመቀበል</u>

ማንኛውም ጠበቃ የሕግ አገልግሎት ለማግኘት የመጣ ደንበኛን ጉዳይ ተቀብሎ የጉዳዩን ፍሬ ነገርና ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ ክርክሩ ሕጋዊ መሠረት የሌለው ከሆነ ጉዳዩን መያዝ የለበትም፡፡ ሆኖም ለሰጠው የሕግ ምክር አገልግሎት ተገቢውን ክፍያ ተቀብሎ ደንበኛውን ያሰናብታል፡፡

27. <u>አገልግሎት ለመስጠት ፈቃደኛ ስላለመሆን</u>

ማንኛውም ጠበቃ በአገልግሎት ጠያቂ ደንበኛው በተፈፀመው ወንጀል ከባድነትና አስነዋሪነት ወይም የደንበኛውን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ የማሕበራዊ ወይም የሞራል አቋሙን መሠረት በማድረግ የጥብቅና አገልግሎት አልሰጥም ማለት አይችልም፡፡

24. **<u>Appeal against the decision of the Bureau Head</u>**

1. The person who is aggrieved by the decision of the Head of the Bureau, where the decision has an error of law, may appeal to the Regional Supreme court within thirty days from receipt of such a decision.
2. The court shall decide on the question of law and directed same to the Head of the Bureau.
3. The Head of the Bureau shall review the case on the basis of the decision of the court.

<u>PART FOUR</u>

<u>Advocates' Code of Conduct</u>

25. **<u>Assisting but not problem creating</u>**

Any advocate shall have the responsibility to assist the organs of the administration of justice in the effort to promote respect for the law and the attainment of justice. Any advocate shall, in particular, discharge his professional duty to his client, other lawyers and opposing party, the court, his profession, and the society in general honestly, faithfully and truthfully.

26. **<u>Receiving Clients</u>**

Any advocate may not handle a case of a client seeking legal service where, after evaluating the facts and the evidence, the claim has no legal ground. However, he may collect reasonable fee for the legal advice he had rendered, and dismiss the client.

27. **<u>Declining Advocacy service</u>**

Any Advocate may not decline to render advocacy service on grounds of the serious and heinous nature of the crime committed, or on the basis of the client's political, economic, social or moral standings.

28. ከደንበኛ ጋር ስለሚደረግ ውል

1. ማንኛውም ጠበቃ ከደንበኛው ጋር በጽሁፍ የሰፈረ ግልጽ የውል ስምምነት ሊፈጽም ይገባል። ውሉም የተዋዋዮችን ስም፣ አድራሻ፣ የአገልግሎቱን ዓይነት፣ የውክልና ዓይነትና መጠን የአገልግሎት ክፍያውን መጠን፣ ክፍያው የሚወሰንበትን ስልትና የአከፋፈሉን ስርዓትና የመክፈያውን ጊዜ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን የያዘ ይሆናል።

2. አንድ ጠበቃ ለደንበኛው የገባውን የሙያ አገልግሎት በአግባቡ ባለማበርከቱ ምክንያት የሚኖርበትን የፍትሐብሔር ኃላፊነት የሚቀንስ ወይም የሚያስቀር ስምምነት ዋጋ የለውም።

29. ብቃት ያለው አገልግሎት ስለመስጠት

1. ማንኛውም ጠበቃ በሚሰጠው የጥብቅና አገልግሎት ከፍተኛ የሙያ ችሎታና ብቃት ማሳየት ይጠበቅበታል።

2. ጠበቃው ሕግ በሚፈቅደው መሠረት፡-

   ሀ. የደንበኛውን መብትና ጥቅም ለማስከበር እውቀቱንና የስራ ልምዱን በስራ ላይ የማዋል፣

   ለ. የደንበኛውን ጉዳይ በትጋት የመከታተልና አፋጣኝና ፍትሐዊ ውሣኔ ለማግኘት ሊወሰድ የሚገባውን እርምጃ ሁሉ በጥንቃቄና በወቅቱ የመፈፀም ሙያዊ ግዴታ አለበት።

30. ምስጢር ስለመጠበቅ

1. ማንኛውም ጠበቃ የደንበኛውን ግላዊ ወይም ድርጅታዊ መረጃ ወይም በሙያ አገልግሎቱ ምክንያት በእጁ የገባውን ማንኛውንም ሌላ መረጃ በምስጢር የመጠበቅ ሙያዊ ግዴታ አለበት።

2. ጠበቃው በውክልናው ምክንያት ከደንበኛው የተሰጠውን መረጃ እና ማንኛውንም ሌላ መረጃ ከደንበኛው ፈቃድ ሣያገኝ ሊገልጽ አይችልም።

28. Contract with client

1. Any advocate shall make a clear and written contractual agreement with his client. The contract shall include the names of the parties, address, type of service, type and scope of representation, the amount of fee, way of computation, mode and time of payment, and such other information as necessary.

2. An agreement restricting or totally avoiding the civil liability of the advocate due to the advocate's failure to render proper service to his client shall be of no effect.

29. Rendering competent service

1. Any advocate is expected to show a high level of professional competence and skill in the advocacy service he renders.

2. Any advocate shall have professional obligation within the limits of the law;

   a. To employ his legal knowledge and work experience to protect the rights and interests of his client;

   b. To follow up his client's case diligently and take all the necessary measures carefully and timely so as to obtaining a quick and just decision.

30. Confidentiality of Information

1. Any advocate shall have professional obligation to keep in secret the personal or organizational information of his client or any other information he obtained in the course of his professional service.

2. The advocate may not, without the consent of the client, reveal information relating to his power of representation and any other information.

3. የጠበቃ ምስጢር የመጠበቅ ሙያዊ ግዴታ በእርሱና በደንበኛው መካከል የነበረው የስራ ውል በመቋረጡ ምክንያት ቀሪ ሊሆን አይችልም፡፡

31. ምስጢር ስለሚገለጽበት ሁኔታ

የዚህ አዋጅ አንቀጽ 32 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ጠበቃው ተገቢ ነው ብሎ ሲያምን በሙያ ስራው አጋጣሚ በእጁ የገባውን መረጃ በሚከተሉት ምክንያቶች እንደአስፈላጊነቱ መጠን ሊገልጽ ይችላል፡-

1. ከደንበኛው ያገኘው መረጃ ለተወከለበት ስራ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ፣
2. ከደንበኛው ጋር ክርክር በሚፈጠርበት ጊዜ ራሱን ለመከላከል ወይም መብቱን ለማስከበር፣
3. የውክልና ስልጣኑን የተመለከተ ክርክር ሲነሣ፣ ወይም
4. ሕግ በሌላ ሁኔታ በግልጽ የጣለበትን ግዴታ ለመወጣት፡፡

32. የጥቅም ግጭት

ማንኛውም ጠበቃ በራሱና በደንበኛው ወይም በቅርብ ዘመዶቹና በደንበኛው ወይም በሽሪኮቹና በደንበኛው ወይም በሁለት ደንበኞቹ መካከል የጥቅም ግጭት መኖሩን እያወቀ የሙያ አገልግሎት ለመስጠት መዋዋል አይችልም፡፡ የጥቅም ግጭት መኖሩ የታወቀው አገልግሎቱ ከተጀመረ በኋላ ከሆነ ይሄንኑ ለደንበኛው አስረድቶ አገልግሎቱን ማቋረጥ አለበት፡፡

33. በጠበቃና በደንበኛ መካከል የሚፈፀሙ ውሎች

ማንኛውም ጠበቃ ከደንበኛው ጋር ማናቸውንም ውል ሊዋዋል የሚችለው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ከተሟሉ ብቻ ነው፡-

1. በጠበቃውና በደንበኛው መካከል የሚደረገው ውል ከወቅቱና ከሁኔታዎች አንጻር ተገቢና ምክንያታዊ ሲሆን፤
2. ጠበቃው የስምምነቶቹን መስፈርቶችና የውሉን ዓይነት ለደንበኛው በግልጽ ያስረዳው ከሆነ፣ ወይም

3. The obligation of professional confidentiality of an advocate may not cease because of termination of the contract with the client.

31. Condition of Disclosure

Without prejudice to the provisions of Article 32 of this proclamation, an advocate may, when he reasonably believes appropriate, reveal to the extent necessary, the information he obtained in the course of his professional duties, in the following cases:

1. When the information he obtained from the client is necessary for the task he is represented;
2. To defend himself or claim his interests in a controversy with the client;
3. When a controversy arises concerning his power of representation; or
4. To perform his obligation as expressly provided otherwise by law.

32. Conflict of interests

Any advocate may not enter into a contract to render professional service when he knows that there exists conflict of interest between the client and himself, or between his relatives and his client, or between his partners and his client, or between his clients. When the existence of conflict of interests has been discovered after the service had already begun, the advocate shall explain the matter to his client and terminate the service.

33. Contracts between Advocate and Client

Any advocate may not enter into, with the client, any contract unless the following conditions are fulfilled:

1. The contract between the advocate and the client is proper and reasonable in view of the time and the situations;
2. The advocate clearly explains to the client the terms of the agreement and type of the contract; or

3. ደንበኛው በውሉ ላይ ከሌላ ሰው ጋር ተማክሮ የተስማማ ሲሆን::

34. <u>በጠበቃና በደንበኛ መካከል ስለሚደረግ ብድር</u>

ማንኛውም ጠበቃ ከደንበኛው ገንዘብ ሊበደር ወይም ለደንበኛው ገንዘብ ሊያበድር አይችልም::

35. <u>የመንግስት ሠራተኛ የነበረ ጠበቃ</u>

1. ማንኛውም ከዚህ ቀደም የመንግስት ሠራተኛ ወይም ባለስልጣን የነበረ ጠበቃ በቀጥታ በወሰንባቸው ወይም በጥልቀት በተሣተፈባቸው ጉዳዮች ላይ ከቀድሞ አሠሪው ጋር ተመካክሮ የጽሁፍ ፈቃድ ካልተሰጠው በስተቀር ለአንድ ደንበኛ የሙያ አገልግሎት መስጠት አይችልም፤

2. ሕግ በግልጽ ካልፈቀደ በስተቀር የመንግስት ሠራተኛ ወይም ባለስልጣን በነበረበት ጊዜ አንድን ግለሰብ በተመለከተ መረጃ ያገኘ ጠበቃ መረጃው ከሚመለከተው ሰው ጥቅም ጋር የሚጻረር ጥቅም ላለው ሰው የጥብቅና አገልግሎት ሊሰጥ አይችልም::

36. <u>የሕግ ሙያ ያልሆኑ ተደራቢ ስራዎች</u>

1. ማንኛውም ጠበቃ በሕግ ሙያ አገልግሎት በተሠማራበት ወቅት ተደራቢ የንግድ ወይም ሌላ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ፖለቲካዊ ስራ የሚያከናውን በሆነ ጊዜ በተደራቢነት የሚሠራው ስራ የሙያውን ታማኝነት፣ ነጻነት ብቃትና ክብር እንዳይቀንሰው ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል::

2. ማንኛውም ጠበቃ ከሙያው ውጪ የሚያከናውነውን ተደራቢ ስራውንና የተሣትፎውን መጠን ለደንበኛው የማስታወቅ ኃላፊነት አለበት::

3. ማንኛውም ጠበቃ ከሙያው ውጪ የሆነ ተደራቢ ስራ በሚሠራበት ወቅት ከደንበኞቹ ጋር የሚያደርገው ግንኙነት ከጥብቅና ሙያው ውጪ መሆኑን በግልጽ እንዲረዱለት ማድረግ ይጠበቅበታል::

4. ማንኛውም ጠበቃ ከጥብቅና ሙያው ውጪ በሆነ ስራ ተሠማርቶ የሚያገኘውን ገቢ በጥብቅና ሙያው ካገኘው ገቢ ለይቶ የሚያሣይ የሂሣብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ አለበት::

3. The client consents to the agreement after consultation with another person.

34. <u>Loans Between Advocate and Client</u>

Any advocate may not lend money to, or borrow money from his client.

35. <u>Advocate who formerly was a Civil Servant</u>

1. Any advocate who formerly was a public employee of officer may not render professional service to a client in matters of which he passed decisions directly or participated in substantially unless he obtains a written consent of the former employer after consultation.

2. Unless otherwise provided by law, an advocate who has acquired information about a person while he was a public employee or officer may not represent a client whose interests are adverse to that person of whom the information is about.

36. <u>Non-Professional subsidiary Activites</u>

1. When an advocate engages in subsidiary commercial or other social, economic, political activities while rendering profesional legal service, he is required to take the nesessory care so that such subsidiary activities may not affect the loyalty, independence, competence and honor of his advocacy profession.

2. Any Advocate shall have the responsibility to notify to his client the subsidiary activites he performs outside his profession and the extent of his participation.

3. Any advocate is required to explain clearly to his clients that he is not acting in his professional capacity when he deals with them in his subsidiary non-professional activities.

4. Any advocate shall keep books of account, which show separetely the income he collects from activities outside his advocacy profession from that he collects from his professional legal service.

37. <u>የደንበኛን ልዩ ፈቃድ ስለማግኘት</u>

ጠበቃ ለደንበኛው በሕግ የተፈቀደለትን የይርጋና ሌሎች ተመሣሣይ መብቶችን በተቃውሞነት በክርክር ወቅት ላያቀርብ የሚችለው ሁኔታውን ለደንበኛው ካስረዳ በኋላ ደንበኛው በጽሁፍ ከፈቀደለት ብቻ ነው::

38. <u>ጉዳዩ በስምምነት እንዲያልቅ ስለመገፋፋት</u>

ጠበቃ የደንበኛው ጉዳይ በፍርድ ቤት ቀርቦ ከሚወሰን ይልቅ በእርቅ ቢያልቅ ተገቢውን ውጤት የሚያስገኝ ሆኖ ባገኘው ጊዜ ጉዳዩ በእርቅ እንዲያልቅ ሊገፋፋ ይችላል::

39. <u>የተከላካይ ጠበቃ ኃላፊነት</u>

1. ማንኛውም ተከላካይ ጠበቃ በደንበኛው ላይ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት የጥፋተኛነት ውሣኔ ሊያሰጥ የሚያበቃ በቂ ማስረጃ መቅረቡን ካላረጋገጠ በስተቀር ደንበኛው በጥፋተኝነት እንዳይቀጣ የመከራከር ግዴታ አለበት::

2. ማንኛውም ጠበቃ ደንበኛው በተከሰሰበት ወንጀል ሙሉ ለሙሉ ጥፋተኛ መሆኑን ማወቁ ወይም በማስረጃነት የሚያቀርባቸው ነገሮች የማያዋጡ መሆናቸውን ማወቁ ለደንበኛው ተገቢውን የክርክር አገልግሎት እንዳይሰጥ ተጽእኖ ሊያሣድር እንደሚችል በመግለጽ ደንበኛውን አስቀድሞ ማስጠንቀቅ ይኖርበታል፤

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ ድንጋጌ ወንጀል ተከሣሽ በቀረበበት ክስ ጥፋተኛ ከመባሉ በፊት እያንዳንዱን የጉዳዩን ነጥብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ጠበቃው የሚያደርገውን ማጣራትና ክርክር አይመለከትም::

40. <u>የሶስተኛ ወገኖችን መብት ስለማክበር</u>

ማንኛውም ጠበቃ ለደንበኛው በሚሰጠው የጥብቅና አገልግሎት ሶስተኛ ወገኖችን ማጉላላት ማዋረድ ወይም በእነዚሁ ወገኖች ላይ ተገቢ ያልሆነ ጫና መፍጠር፣ ሌላ መሠረታዊ ግብ በሌለው ወይም የሶስተኛ ወገኖችን ሕጋዊ መብት በሚጋፋ መንገድ ማስረጃ የማግኘት ዘዴ መጠቀም የለበትም::

37. **<u>Obtaining Client's Special consent</u>**

An advocate may decline to raise, as an objection in a proceeding, period of limitation and similar other Rights provided by the law to the client and the client consents thereto in writing.

38. **<u>Encouraging the considration of a case by settlement</u>**

When an advocate finds that the desired result can be obtained if his client's case can be resolved by settlement rather than in court, he may encourage the consideration of the case by settlement.

39. **<u>Responsibilities of a Defense Advocate</u>**

1. Any defense advocate shall have the obligation to defend his client unless he is certain that adequate evidence has been produced to establish the guilt of the client by the court, which has the authority.

2. Any advocate is required to warn his client before hand the fact that the advocate's knowledge that the client is guilty or that the things to be produced as evidences are not reliable may affect the advocate in giving the proper defense service to the client.

3. The porvisions of sub article (2) of this article shall not affect the inquiry and defense to be made by an advocate to ascerain that every element of the case be established before an accused in a criminal proceeding is held responsible.

40. **<u>Respect for Rights of third parties</u>**

In repesenting a client, an advocate may not use means to have no substantial purpose other than to delay, embarras or burden third parties, or sue methods of obtaining evidence that violate the legal rights of such persons.

41. የጥብቅና አገልግሎት ስለማቋረጥ

1. ማንኛውም ጠበቃ ለደንበኛው ሊሰጥ የሚገባውን የጥብቅና አገልግሎት ውል ለማቋረጥ የሚያስችል በቂና አሳማኝ ምክንያት ከሌለው በስተቀር በገባው የውል ግዴታ መሠረት የደንበኛውን ጉዳይ እስከመጨረሻው የመከታተል ግዴታ አለበት፡፡

2. ጠበቃው ለደንበኛው በገባው የውል ግዴታ መሠረት የደንበኛውን ጉዳይ እስከመጨረሻው ለመከታተል ባልቻለ ጊዜ ሁኔታውን ለደንበኛው የመግለጽና አገልግሎቱን በማቋረጡ ምክንያት በደንበኛው ላይ ሊደርስ የሚችለውን ወጪና መጉላላት ለመቀነስ እንዲሁም ጉዳዩ በተቃና ሁኔታ በሌላ ጠበቃ ሊሸፈን የሚችልበትን ሁኔታ የማመቻቸት ግዴታ አለበት፡፡

42. አገልግሎት ለማቋረጥ በቂ ምክንያቶች

ጠበቃ ለደንበኛው የሚሰጠውን አገልግሎት ለማቋረጥ የሚያስገድዱት በቂ ምክንያቶች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፡-

1 የተፈለገው የጥብቅና አገልግሎት ይህንን አዋጅ ወይም ሌላ ሕግ የሚጥስ ከሆነ፣

2. ጠበቃው የተወከለበት ጉዳይ በመታየት ላይ ባለበት ወቅት ደንበኛው በጉዳዩ አካሄድ ላይ ተገቢ ያልሆነ ከሆነና ከጠበቃው የሚያገኘውን አገልግሎት ለወንጀል ወይም ለማታለል ድርጊት ከተጠቀመበት ወይም ክርክሩን በሌላ ሰው ላይ መጉላላትን ለማስከተል ወይም ጉዳት ለማድረስ የተጠቀመበት ከሆነ፣

3. ጠበቃው ጉዳዩን በአግባቡ ለመምራት ችሎታና ብቃት ያነሰው እንደሆነ ወይም ከጥብቅና ስራው ከተወገደ፣

4. ደንበኛው ውክልናውን በተመለከተ ከጠበቃው የሚፈለግበትን ግዴታ ሣይወጣ ሲቀር እና ግዴታውን ካልፈፀመ አገልግሎት የሚያቋርጥ መሆኑን ጠበቃው ካስጠነቀቀው፣

5. በጠበቃውና በደንበኛው መካከል ሊኖር የሚገባው መተማመን አንዱ ወገን የማታለል ወይም የማጭበርበር ድርጊት በመፈጸሙ የተነሣ በከፍተኛ ሁኔታ የተናጋ ከሆነ፣

41. Terminating Advocacy Service

1. Unless there is sufficient and convincing reason to terminate the contract of advocacy service, an advocate shall have the obligation to follow his client's case up to the end in accordance with his obligation in the contract.

2. When the advocate is not able, as the contract obliges him, to follow his client's case up to the end, he shall explain the matter to his client and shall have the obligation to make the necessary effort to minimize the cost and inconvenience that would be caused as a result of the termination and to get the matter be successfully covered by another advocate.

42. Sufficient Grounds for Termination

Sufficeient grounds to terminate representation include, among others, the following when:

1. The client's required advocacy service is in violation of this proclamation or other law;

2. While in the course of trial of the matter for which the advocate is represented the client commits an act which is repugnant to the proceeding, the client has used the advocate's service to perpetrate a crime or fraud or the client has used the proceeding to cause inconvenience or cause damage on other person;

3. The advocate lacks the competence and ability to properly manage the case or he is discharged from his profession;

4. The client fails to fulfill an obligation to the advocate regarding the representation and has been given notice by the advocate that will terminate the service unless the obligation is fulfilled;

5. The mutual trust that should have been present between the advocate and the client has been greatly damaged due to fraud or deceit committed on the part of either party;

6. የጉዳዩን ሂደት በሚመለከት ጠበቃው ወሣኝ በሆኑ ነገሮች ላይ የሚሰጠውን የሕግ ምክር ደንበኛው ውድቅ በማድረጉ የተነሣ በሁለቱ ወገኖች መካከል ሊኖር የሚገባው መተማመን ከጠፋ፣

7. ደንበኛው ለጠበቃው መክፈል ያለበትን የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፍልና ሌሎችንም ወጪዎች እንዲተካ ተገቢው ማሳሰቢያ ተሰጥቶት ኃላፊነቱን ለመወጣት ፈቃደኛ አለመሆኑን በግልጽ ካሣየ።

43. አገልግሎት የሚያቋርጥ ጠበቃ ግዴታዎች

ማንኛውም ጠበቃ ውል ሲያቋርጥ የሚከተሉትን ግዴታዎች መወጣት አለበት፡-

1. ለደንበኛው ማስታወቂያ መስጠት እና ደንበኛው ሌላ ጠበቃ እንዲወክል በቂ ጊዜ መስጠት፣
2. የደንበኛውን ንብረትና ሠነዶች ስርዓት ባለው መንገድ ወዲያውኑ ማስረከብ፣
3. ስለ ጉዳዩ ደንበኛው የሚጠይቀውን ማንኛውንም መረጃ መስጠት፣
4. በደንበኛው እጅ የሚገኘን ማንኛውንም ሂሣብ መተሳሰብና ወደፊት ለሚሠራ ስራ የተቀበለውን ገንዘብ ከወጪ ቀሪውን ተመላሽ ማድረግ፣
5. ለስራ ማስኬጃ የተረከባቸውን ሂሣቦች በመተሳሰብ ከወጪ ቀሪ መመለስ፣
6. ከተተኪው ጠበቃ ጋር በመተባበር በጉዳዩ መጓተት፣ መቋረጥ ወይም አላስፈላጊ ወጪ እንዳያጋጥመው መከላከል።

44. የተተኪ ጠበቃ ግዴታዎች

1. ተተኪው ጠበቃ ደንበኛው ከቀድሞ ጠበቃው ጋር ያለውን ማንኛውንም ሂሣብ እንዲያወራርድ ማሳሰብ ይጠበቅበታል፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተው ደንበኛው ለቀድሞ ጠበቃው መክፈል ያለበትን የአገልግሎት ክፍያ አለማጠናቀቁ አዲሱ ጠበቃ በቀጠሮ ቀን በፍርድ ቤት ተገኝቶ ተገቢውን አገልግሎት እንዳይሰጥ ሊያግደው አይችልም።

6. The mutual trust that should have been present between the two parties has been weakend because the client denounces the advice given by his advocate on matters that are decisive to the case;

7. The client shows clearly that he is not willing to fulfill his obligation to pay fees and reimburse other expenses to the advocate, after he has been given the proper notice.

43. Obligation of an Advocate on Termination of Advocacy Service

Any advocate terminating contract of advocacy service shall fulfill the following obligations:

1. Give reasonable notice to the client and reasonable time to allow the client represent other advocate;
2. Properly surrender the property and records of the client immediately;
3. Give any information the client requests regarding the case;
4. Audit any account found in the client's hands, return the money left from payment received for a future work;
5. Audit the accounts he received in advance for the management of the case and return the money left;
6. In cooperation with the replacing advocate, protect the case against delay, interruption or unnecessary expenses.

44. Obligations of Replacing Advocate

1. The replacing advocate is required to inform his client to audit any account the client has with the former advocate.
2. The provisions of sub article (1) of this article that the client has not completed the fee to be paid to the former advocate shall not prohibit the new advocate from rendering the proper service on the fixed date, in court.

45. የሕግ አገልግሎት ድርጅት አባል ስለመሆን

ማንኛውም ጠበቃ የጥብቅና አገልግሎት ድርጅት አባል ለመሆን ይችላል::

ጠበቃው አባል የሆነበት ድርጅት በሚሠጣቸው ውሣኔዎች ወይም በሚወስዳቸው እርምጃዎች ላይ መካፈል የማይችለው:-

1. በውሣኔው ተካፋይ መሆኑ ከደንበኛው ጥቅም ጋር የሚጋጭ ሲሆን፣
2. አገልግሎት የሚሰጠው ሰው ወይም ማሕበረሰብ ከጠበቃው ወይም ከጠበቃው ደንበኛ ጋር የማይጣጣም ጥቅምና ፍላጐት ያላቸው ሲሆን::

46. <u>በሽሪክ ወይም በተቆጣጣሪ ጠበቃ ስለሚሰጥ የጥብቅና አገልግሎት</u>

1. የጥብቅና ድርጅት ሽሪክ የሆነ ጠበቃ በድርጅቱ ውስጥ የሚሠራ ማንኛውም የሕግ ባለሙያ ይህንን አዋጅ ማክበሩን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፣
2. ማንኛውም ሌላውን ጠበቃ በቀጥታ የመቆጣጠር ስልጣን ያለው ጠበቃ በእርሱ ስር የሚያገለግል ጠበቃ ይህንን አዋጅ ማክበሩን የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት::
3. ማንኛውም ጠበቃ ሌላው ጠበቃ ለሚፈጽመው የዚህ አዋጅ መተላለፍ ተጠያቂ የሚሆነው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው:-
   - ሀ. ጥፋት የፈፀመው ሰው ድርጊቱን የፈፀመው በጠበቃው ታዝዞ ሲሆን ወይም ጉድለት እየተፈፀመ መሆኑን እያወቀ ድርጊቱን ያፀደቀው ሲሆን፣
   - ለ. ጥፋት የፈጸመው ሰው ጠበቃው በሚሠራበት የጥብቅና አገልግሎት ድርጅት ሽሪክ ከሆነ ወይም በጠበቃው ቀጥተኛ ቁጥጥር ስር የሚሠራ ከሆነና ግለሰቡ በዚህ አዋጅ የሚያስቀጣ ድርጊት እየፈጸመ መሆኑን እያወቀ ድርጊቱ የሚያስከትለውን የማስተካከያ እርምጃ ያልወሰደ ሲሆን::

45. <u>Membership in Legal Services Organization</u>

Any advocate may be a member in a legal service organization. The advocate may not participate in decisions or actions of the organization where he is a member if:

1. His participation in the decision or action would conflict with the interest of his client;
2. The person or community which receives service has interests that are not compatible with the interest of the advocate or his client.

46. <u>Advocacy Service Rendered by a Partner or Supervisory Lawyer</u>

1. An advocate who is a partner in law firm shall ensure that any other lawyer in the firm conforms to this proclamation;
2. Any advocate who has supervisory authority over another advocate shall have the responsibility to supervise that the other advocate conforms to this proclamation;
3. An advocate shall be responsible for another advocate's violation of this proclamation if :
   - a. The lawyer orders or, with the knowledge of the conduct, ratifies it,
   - b. While the person at fault is a partner of the advocate or works under the direct supervision of the advocate, the advocate knows of the punishable conduct at a time when its consequences can be avoided or mitigated but fails to take reasonable remedial action.

47. ክልከላ

1. በማንኛውም የጥብቅና አገልግሎት ድርጅት ውስጥ የሚሠራ ጠበቃ በድርጅቱ ውስጥ ከሚሠሩት ሌሎች ጠበቆች አንዱ በዚህ አዋጅ መሠረት አንድን ጉዳይ በጥብቅና ለብቻው ከመያዝ የሚያግደው ምክንያት መኖሩን እያወቀ የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት አይችልም::

2. የሚከተሉት ሁኔታዎች ካላጋጠሙ በስተቀር የጥብቅና አገልግሎት ድርጅትን የለቀቀ ጠበቃ በድርጅቱ ውስጥ በነበረበት ጊዜ ወክሎት ከነበረ ደንበኛ ጥቅም ጋር የሚጋጭ ጥቅም ያለው ደንበኛን ድርጅቱ ከመወከል አያግደውም:-

   ሀ. ጉዳዩ ከዚህ ቀደም ለድርጅቱ የቀረበ ወይም ከቀድሞው ጉዳይ ጋር መሠረታዊ በሆነ መንገድ የተያያዘ ከሆነ፣

   ለ. በጥብቅና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቱ ውስጥ ያለ ጠበቃ በቀረበው ጉዳይ ላይ በማስረጃነት ሊያገለግል የሚችል መረጃ በእጁ የሚገኝ ከሆነ::

3. በዚህ አንቀጽ የተጣለው ክልከላ ጉዳይ የሚመለከተው ደንበኛ ክልከላው ተፈጻሚ እንዳይሆን በጽሁፍ በተስማማ ጊዜ ቀሪ ይሆናል::

48. የበታች ጠበቃ ግዴታ

1. በሌላ ጠበቃ አመራር ስር የሚሠራ ማንኛውም ጠበቃ ይህንን አዋጅ ማክበር አለበት::

2. የበታች ጠበቃ አከራካሪ በሆነ የሥነ ምግባር ጥያቄ ላይ የበላዩን ትእዛዝ በመቀበል የሠራ መሆኑን ለማስረዳት በቻለ ጊዜ ከተጠያቂነት ነጻ ይሆናል::

49. የሕግ ሙያተኛ ያልሆኑ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን ስለመቆጣጠር

የሕግ ባለሙያ ያልሆነን ሰው በተቀጣሪነት ወይም ለሚሰጠው አገልግሎት የተወሰነ ክፍያ በመስጠት ወይም በተባባሪነት የሚያሠራ ጠበቃ ወይም የጥብቅና አገልግሎት ድርጅት:-

47. Disqualification

1. Any advocate who is working in an advocacy firm may not render service when he knows that there is a reason, in accordance with this proclamation, that would prohibit any of other advocates in the firm to handle the matter alone.

2. The firm is not prohibited from thereafter representing a person with interests adverse to those of a client represented by the formerly associate advocate unless the following conditions are met :

   a. The matter has been presented to the firm before or is substantially related to the formerly dealt matter by the firm;

   b. An advocate remaining in the firm has information in his hands that can be used as evidence on the matter.

3. The disqualification imposed by this article may be waived when the client involved in the matter consents to its application in writing.

48. Obligations of a subordinate Advocate

1. Any advocate who is acting at the order of another advocate shall respect this proclamation.

2. A subordinate advocate shall be free from being responsible when he proves that he acted in accordance with the direction of his superior on an arguable ethical question.

49. Supervision of Non-Lawyer Assistants to Advocate

An advocate or advocacy firm who employs or retains or associated with a person who is a non-lawyer shall:

1. ተገቢውን የጥንቃቄ እርምጃና ተፈላጊውን ቁጥጥር በማድረግ የግለሰቡ ሥነ ምግባር ይህንን አዋጅ እንዳይጥስ ይቆጣጠራል፣

2. የሕግ ሙያተኛ ያልሆነው ባልደረባ ለፈፀመው የሥነ ምግባር ጉድለት ጠበቃው ተጠያቂ የሚሆነው:-

ሀ. ድርጊቱን እንዲፈጸም ያዘዘው ከሆነ ወይም የተፈፀመውን ድርጊት የሚያውቅ ከሆነና አፈጻጸሙንም የፈቀደ ወይም ያፀደቀ ከሆነ፣

ለ. ሙያተኛ ባልሆነው ሰው ላይ የቁጥጥር ስልጣን ኖሮት የሥነ ምግባር ጉድለት የሆነውን ድርጊት መፈጸሙን እያወቀና ድርጊቱ የሚያስከትለውን ውጤት ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ እየቻለ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ያልወሰደ ከሆነ ነው::

50. የአገልግሎት ክፍያ ስምምነት

1. የአገልግሎት ክፍያ ስምምነት በጽሁፍ የሚደረግና በተዋዋይ ወገኖች ወይም በወኪሎቻቸው የሚፈረም ሕጋዊ ሰነድ ነው::

2. በጠበቃና በደንበኛ መካከል የሚፈጸም የአገልግሎት ክፍያ ስምምነት የሚከተሉትን መሠረታዊ ጉዳዮች ይወስናል:-

ሀ. ደንበኛው ለጠበቃው የሚከፍለውን አጠቃላይ ገንዘብ፣ ደመወዝ፣ የማካካሻ ክፍያ፣ የመጠባበቂያ ክፍያ ወይም ሌላ የክፍያ ስርዓት በመግለጽ የአከፋፈሉን ስልትና ጊዜ፣

ለ. ጠበቃው በጉዳዩ ላይ የሚያስገኘውን የውጤት ዓይነት ወይም ዓይነቶች::

51. መጠኑ ያልተወሰነ የአገልግሎት ክፍያ ስምምነት

የአገልግሎት ክፍያው ክርክሩ በሚያስገኘው የገንዘብ መጠን ላይ የተመሠረተ በሆነ ጊዜ ስምምነቱ የሚከተሉትን መሠረታዊ ጉዳዮች የያዘ ይሆናል:-

1. Supervise that the person's conduct is compatible with this proclamation by taking the appropriate measures and making the necessary supervision;

2. Be responsible for unethical conduct committed by the non-lawyer and with the knowledge of the commission of the act he fails to take the appropriate remedial action to avoid or mitigate the consequences of the act.

a. The advocate orders the commission of the act, or with the knowledge of the act, ratifies or allows the act,

b. While having a supervisory authouity over the non-lawyer and with the knowledge of the commission of the act, he fails to take the appropriate remedial action to avoid or mitigate the consequences of the act.

50. Fee Agreement

1. An agreement of fee is a legal document to be made in writing and signed by the parties to the agreement or their representatives.

2. A fee agreement to be made between advocate and client determines the following basic matters:

c. The total amount of money, salary, reimbursement, reserve payment or other mode of payment to be made by the client and the method and time of payment.

d. The kind of result or results to be obtained from the case by the advocate.

51. Contingent fee Agreement

When the fee is contingent on the amount of the money obtained from the litigation, the agreement shall be determined based on the forllowing basic matters:

1. ጉዳዩ በስምምነት፣ በይግባኝ ወይም በሌላ መንገድ ቢያልቅ ከእነዚህ ሁኔታዎች በአንዱ ደንበኛው ከሚያገኘው ገንዘብ ላይ ለጠበቃው በመቶኛ ስሌት ሊከፈለው የሚገባውን የገንዘብ መጠን፣
2. ለጠበቃው የሚደርሰው ሂሣብ የዳኝነት ክፍያና ሌሎች ወጪዎች ከተቀናነሱ በኋላ የሚታሰብ ወይም ከአጠቃላዩ ገንዘብ የሚታሰብ መሆኑን::

52. መጠኑ ያልተወሰነ የአገልግሎት ክፍያ የማይጠየቅባቸው ጉዳዮች

ጠበቃ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ያልተወሰነ የአገልግሎት ክፍያ ስምምነት ሊያደርግ አይችልም:-

1. በመደበኛ ፍ/ቤት በባልና ሚስት ክርክር ፍችን በማስገኘት ላይ ተመስርቶ ወይም በሚያስወስነው የቀለብ ወይም የልጆች ማሳደጊያ ገንዘብ ወይም በሚያስገኘው የንብረት መጠን፣
2. በወንጀል በተከሰሰ ሰው ላይ ፍርድ ቤት በሚሰጠው ውሣኔና ቅጣት ላይ ተመርኩዞ::

53. ነጻ የሕግ አገልግሎት ስለመስጠት

ማንኛውም ጠበቃ በነጻ በዓመት ቢያንስ ለ50 ሰዓታት የሕግ አገልግሎት መስጠት አለበት:: አገልግሎት የሚሰጠውም:-

1. የመክፈል አቅም ለሌላቸው ሰዎች፣
2. ለበጐ አድራጐት ድርጅቶች፣ ለሲቪክ ድርጅቶች ወይም ለማሕበረሰብ ተቋማት፣
3. ፍ/ቤት የጥብቅና አገልግሎት እንዲያገኙ ለሚጠይቅላቸው ሰዎች፣
4. ሕግን፣ የሕግ ሙያንና የፍትሕ ስርዓትን ለማሻሻል ለሚሠሩ ኮሚቴዎችና ድርጅቶች::

1. The percentage that shall be paid to the advocate in each individual event if the case is resolved by settlement, appeal or other means;
2. Whether the amount that has to accrue to the advocate is calculated after court fees and other expenses are deducted or from the gross amount.

52. Cases of Prohibition of Contingent Fee

An advocate may not enter into an agreement for contingent fee on the following matters:

1. In a family matter contingent upon the securing of a divorce or upon the decision on the amount of alimony or supprot for the upkeep of the children or property settlement in a court of law;
2. A fee contingent upon the decision and penality given by the court in a criminal case.

53. Rendering free Legal Services (Pro Bono Publico Service)

Any advocate shall render at least 50 hours of legal service, in a year, free of charge. The service shall be rendered to:

1. Persons who can not afford to pay;
2. Charity organizations, civic organizations or community institutions;
3. Persons to whom court requests legal service;
4. Committees and institutions that work for improving the law, the legal profession and the justice system.

54. <u>የጥብቅና አገልግሎትን አስመልክቶ ስለሚሰጥ መግለጫ</u>

ማንኛውም ጠበቃ ስለ እራሱ ወይም ስለሚሰጠው አገልግሎት ሀሰተኛ ወይም የሚያሳስት መግለጫ መስጠት የለበትም። ከጠበቃ የሚሰጥ መግለጫ ሀሰተኛ ወይም የሚያሳስት ነው ሊባል የሚችለው:-

1. አንድ ፍሬ ነገር ወይም ሕግ ያልሆነውን እንደሆነ አድርጐ ካቀረበ ወይም ፍሬ ነገሩን በመደበቅ አንድን አባባል እውነት አስመስሎ ካቀረበ፤
2. ጠበቃ በክርክር ሊያስገኘው የሚችለውን ውጤት አጋኖ በማቅረብ ተገቢ ያልሆነ ተስፋ እንዲፈጠር ከገፋፋ ወይም ይህንን አዋጅ የሚጥስ ዘዴን በመጠቀም ለጉዳዩ ውጤት ለማስገኘት ቃል የገባ ሲሆን፤
3. በተጨባጭ ማረጋገጥ የሚቻል ካልሆነ በስተቀር አንድ ጠበቃ የራሱን የጥብቅና አገልግሎት ከሌሎች ጠበቆች አገልግሎት ጋር በማነጻጸር የራሱን አጉልቶ የሚያሣይ መግለጫ ከሰጠ ነው።

55. ደንበኛን አስመልክቶ ስለሚሰጥ መግለጫ

ማንኛውም ጠበቃ የደንበኛውን ጉዳይ አስመልክቶ ለሶስተኛ ወገኖች በፍሬ ጉዳዩም ሆነ በሕግ ረገድ ሀሰተኛ የሆነ መረጃ መስጠት አይችልም።

56. <u>ማስታወቂያ ስለማውጣት</u>

1. ማንኛውም ጠበቃ የሚሰጠውን የሕግ አገልግሎት በሚለጠፍ ማስታወቂያና በሌሎች መገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች ማስተዋወቅ ይችላል። ማስታወቂያው አጭር፣ ግልጽና ትክክለኛ ሆኖ የጠበቃውን ስም፣ አድራሻ፣ የሚሰጠውን አገልግሎትና የሥራ ልምድ መግለጽ ይኖርበታል።
2. ማንኛውም ጠበቃ ማስታወቂያውን ለመገናኛ ብዙኃን ከመላኩ ከሠላሣ ቀናት በፊት ለጥብቅና ሥራ ፈቃድ ሰጪው አካል አንድ ኮፒ እንዲደርሰው ማድረግ አለበት።
3. በዚህ አንቀጽ መሠረት ለሚዘጋጅ ማስታወቂያ ይዘት ተጠያቂ የሚሆን ቢያንስ የአንድ ጠበቃ ስም መጨመር አለበት።

54. **<u>Communications Concerning Advocate</u>**

An advocate may not give false or misleading communication about himself or his services. A communication given by an advocate is false or misleading if it:

1. Contains a material misrepresentation of fact or law or omits a fact to make a statement considered true;
2. Creates an unjustified expectation about the results the advocate can achieve by exaggerating the possible results or the advocate promises that he can achieve results by means that violate this proclamation;
3. Compares the services he renders with other advocate's services unless the comparison can be factually substantiated.

55. **<u>Truthfulness in Statement to others</u>**

Any advocate may not give a false statement of material fact or law to a third person concerning his client.

56. **<u>Advertising</u>**

1. Any advocate may advertise the legal services he renders through outdoor advertising or other mass media. The advertisement shall be brief, clear and correct and shall contain the name and address of the advocate and, the service he renders and work experience.
2. Any advocate shall give a copy of the advertisement to the body that issues advocacy license 30 days before the advertisement is sent to mass media.
3. An advertisement prepared pursuant to this article shall include the name of, at least, one advocate responsible for its content.

57. የሙያ ባልደረባን ስለማክበር

1. ማንኛውም ጠበቃ ከሌሎች የሙያ ባልደረቦቹ ጋር የሚኖረው ግንኙነት በቅን ልቡና፣ በመከባበርና በመግባባት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ማድረግ አለበት።
2. በፍትሕ መድረክ የሙያ ባልደረባን መዝለፍ፣ ማንቋሸሽ ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ ክብሩን ለመቀነስ መሞከር የተከለከለ ነው።
3. ማንኛውም ጠበቃ ከደንበኛው ወይም ከሌላ ጠበቃ ጋር የሚያደርገውን ንግግር ለመቅረጽ የሚፈልግ መሆኑን አስቀድሞ ሳያሳውቅ መቅረጽ የለበትም።
4. ማንኛውም ጠበቃ ከሙያ ባልደረባው ለሚደርሱት የስራ ግንኙነት ደብዳቤዎች ተገቢውን ምላሽ የመስጠትና ይህን ግንኙነት አስመልክቶ የተደረገውን ስምምነት የማክበር ግዴታ አለበት።
5. የተለየ ስምምነት ካልተደረገ በስተቀር አንድ ጠበቃ የተከራካሪው ወገን ጠበቃ ሳያውቀው ወይም እርሱ በሌለበት ከተከራካሪው ጋር መደራደር የለበትም።

58. በክርክር ወቅት የጠበቃ ግዴታዎች

ማንኛውም ጠበቃ በክርክር ወቅት የሚከተሉትን ድርጊቶች ከመፈጸም መቆጠብ አለበት፡-

1. በክፉ ልቡና ተነሳስቶ ሌላውን ወገን የሚጎዳ ክስ ወይም ክርክር ማቅረብ፣
2. ደንበኛው የማጭበርበር ድርጊት እንዲፈጽም ማበረታታት ወይም መፍቀድ፣
3. ዳኛን ወይም ሌላ የፍ/ቤት ሠራተኛን በሕግ መሠረት ከማሳመን ውጪ ሌላ ተገቢ ያልሆነ ማንኛውንም ዓይነት ዘዴ በመጠቀም ተጽእኖ ለማሳደር መሞከር ወይም በሌላ ሰው እንዲሞከር ማድረግ፣
4. ሆን ብሎ ፍ/ቤትን የሚያሳስት ወይም የተጋነኑ ጽሁፎች ማቅረብና ንግግር ማድረግ፣
5. በምስክርነት ቃል ወይም የሠነድ ይዘት ላይ የሀሰት ድርጊት በመፈጸም ፍርድ ቤትን ለማሳሳት መሞከር፣

57. Respect for colleagues

1. Any advocate shall make sure that his relations with other professional colleagues are based on good faith, respect and understanding.
2. It is prohibited to insult, belittle or in any otherway attack the reputation of a fellow advocate in the justice forum.
3. Any advocate may not record the dialogue he holds with his client or other advocate without notifying them of his intention to do so.
4. Any advocate shall reply to letters of correspondence from his colleague and respect the agreement he entered into on this matter.
5. Any advocate may not sit for settlement in the absence of the opposing party's advocate without the knowledge of the said advocate, unless otherwise agreed.

58. Obligations of Advocate in Proceedings

Any advocate shall refrain from the following acts in a proceeding:

1. Institute a case or forward a litigation motivated by envy or badfaith to injure the other party;
2. Encourage or allow a client to commit a fraudulent act;
3. Attempt to influence a judge or other official by means not acceptable other than to convince according to the law or seek the act to be done by another person;
4. Intentionally make papers and statements which are exaggerated, mislead the court; or
5. Intentionally mislead the court by falsifying the testimonies of witnesses or the contents of a document;

6. በግልጽ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ማስረጃ አግባብነት ያለው አስመስሎ ለፍርድ ቤት ማቅረብ፣

7. ለጉዳዩ በምስክርነት መቅረብ የሚገባው ሰው ፍርድ ቤት እንዳይቀርብ ማባበል ወይም መሞከር፣

8. አንድን ምስክር ተገቢ ባልሆነ መንገድ ማመናጨቅ፣ ማስጨነቅ ወይም ማስፈራራት።

59. የሥነ ምግባር ጉድለት መፈጸሙን ስለማሳወቅ

ማንኛውም ጠበቃ ከዚህ በታች የተመለከቱት መፈፀማቸውን እንዳወቀ ድርጊቱን የፈፀመውን ሰው ስምና የጥፋቱን ዓይነት በመግለጽ ለፈቃድ ሰጪው አካል ወይም በአካባቢው ለሚገኘው የፍትሕ አስተዳደር ባለስልጣን የማስታወቅ ግዴታ አለበት፡-

1. አንድ ጠበቃ ይህን አዋጅ ጥሶ ከተገኘ፣

2. አንድ ሰው የጥብቅና ሥራ ፈቃድ ሣይኖረው የጥብቅና አገልግሎት ሲሰጥ ከተገኘ፣ ወይም

3. አንድ ጠበቃ በጥብቅና ሥራ ፈቃዱ ከተፈቀደለት ውጪ ሲሠራ ከተገኘ።

ክፍል አምስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

60. የጠበቃው ግዴታዎች

ማንኛውም ጠበቃ፡-

1. ይህንን አዋጅ እንዲሁም በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጡትን ትእዛዞችና ውሣኔዎች የማክበር፣

2. ከደንበኛው ለሚቀበለው ማንኛውም ዓይነት ክፍያ ደረሰኝ የመስጠት፣

3. ፈቃድ ሲያወጣና ሲያሳድስ እንዲሁም ፈተና ሲወስድ መክፈል ያለበትን ክፍያ መክፈልና የነጻ ግልጋሎት የሰጠበትን ማስረጃም ሆነ ሌሎች አስፈላጊ ማስረጃዎችን የማቅረብ ግዴታ አለበት።

6. Produce to court as though relevant an evidence which is clearly irrelevant to the matter;

7. Counsel or induce a person who is required as a witness, not to appear before court;

8. Nag, traumatize or threaten a witness in methods that are inappropriate.

59. Notifying unethical conduct

Any advocate on kowledge of the following violation shall have the obligation to notify to the body issuing advocacy license or to the local justice administration authority as to the name of the advocate and the type of the violation:

1. Where an advocate violates this proclamation;

2. Where a person renders legal service without having advocacy license;

3. Where an advocate is found rendering advocacy service beyond the scope expressed in the license.

PART FIVE

Miscellaneous Provisions

60. Duties of the advocate

Any advocate shall have the duty to:

1. Observe this proclamation and respect orders and decisions thereof;

2. Give a receipt in respect of any consideration he receives from his client;

3. Pay the fees required in obtaining, renewing and replacing a license, and produce evidence of free advocacy service and other essential evidences when necessary.

61. <u>ስለቅጣት</u>

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የበለጠ ቅጣት የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ ሳያወጣ ወይም የጥብቅና ሥራ ፈቃዱን ሳያሳድስ የጥብቅና አገልግሎት የሰጠ ወይም ለመስጠት የሞከረ እንደሆነ ከብር 2ሺ. በማያንስና ከብር 10 ሺ. በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከስድስት ወር በማያንስና ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል::

62. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8፣ 9 እና 10 ሥር የሰፈሩት ድንጋጌዎች ቢኖሩም ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በክልሉም ሆነ በፌደራሉ መንግስት የሚሰጠውን የጥብቅና ሥራ ፈቃድ ይዘው በክልሉ ውስጥ ግልጋሎት ሲሰጡ ለነበሩ ጠበቆች ቢሮው እንዳስፈላጊነቱ ያለፈተና ወይም ፈተና በመስጠት የክልል አንደኛ ደረጃ ወይም ሁለተኛ ደረጃ የጥብቅና ሥራ ፈቃድ ሊሰጣቸው ይችላል::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ቢሮው በዚህ አዋጅ መሠረት የጠበቆችን ፈቃድ ጉዳይ ማስተናገድ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ የክልሉ የጥብቅና ሥራ ፈቃድ እንዲሰጠው ያላመለከተ ማንኛውም ጠበቃ ከዚህ በፊት የተሰጠ ፈቃድ እንደሌለው ተቆጥሮ የክልል ጉዳዮችን አስመልክቶ በክልል ፍ/ቤቶች ጥብቅና ለመቆም በዚህ አዋጅ የተደነገገውን መስፈርት አሟልቶ አዲስ ፈቃድ እንዲያወጣ ይገደዳል::

63 <u>ደንብ የማውጣት ስልጣን</u>

ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን ደንቦች የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሊያወጣ ይችላል::

64. <u>ስለተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም::

61. **<u>Penalties</u>**

Unless the provisions of the penal code provide a more severe penalty, any person who renders or attempts to render advocacy services without having obtained a license, or renewing his license in accordance with this proclamation shall be punished with a fine not less than birr 2,000 and not exceeding birr 10,000 or imprisonment not less than 6 months and not exceeding two years.

62. **<u>Transitory Provisions</u>**

1. Without prejudice to the provisions of Article 8,9, and 10 of this proclamation, Advocates who have been rendering advocacy services in the region after having obtained license from the Regional or Federal government, prior to the issuance of this proclamation, may obtain first class or second class license with or without entry examination as the case may be.

2. Notwithstanding the provisions of sub article (1) of this Article, any advocate who fails to apply for advocay license of the Region within 6 months following the commencement of the issuance of license by the Bureau, may be required to sit for an entry examination, if he lateon applies for Reginal license.

63. **<u>Powers to issue Regulations</u>**

The Council of Regioal Government issue regulations necessary for the implementation of this proclamation.

64. **<u>Repealed and Inapplicable Laws</u>**

Any law , regulation , directive, or practice inconsistent with the provisions of this proclamation may not be applicable to matters covered under this proclamation.

65. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በክልሉ ዝክረ ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር
ነሐሴ 4 ቀን 1994 ዓ.ም

ዮሴፍ ረታ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ፕሬዚዳንት

65. **Effective Date**

This proclamation shall enter into force as of the date of its publication in the Zikre Hig Gazette of the Region.

Done at Bahir Dar,
this 10th day of August,2002.

Yosef Retta
President of the Amhara National
Region